## የኢሕአፓው አመራር አባል ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ



## <u>ተስፋዬ ተስፋ ሁነን</u>

(39ኛውን የሙት ዓመት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ ከ«ያ ትውልድ ተቋም»)

በዕለተ ሐሙስ ፣ ወርሃ መጋቢት
በወሩ አጋማሽ ፣ ልክ በአሥራ አምስት
ሺህ ዘጠኝ መቶ 69 ዕለት
ሺህ ሰው አሸለበ ፣ ባንድ ጀግና እልፈት።
የትግል ዓርማ ዝቅ አለ ፣ ሰማዩ ደመነ
ዕምባዎች ጐረፉ ፣ ትግል ሀዘን ሆነ።
አየሩ በረደ ፣ ዝቅ አሉ መፈክሮች
ህዋሳት ፈዘዙ ፣ ተወጉ ስሜቶች።
ኢሕአፓን መታው ሀዘን ፣ ብርሃን ጨለመ
የትግል ሕይወቱ ፣ እጅጉን ታመመ
ተቀማ መሪውን ፣ ሩቅ አሳቢውን
ባጭሩ ቀጠፉት ፣ ዕምቡጥ አበባውን።
ከራሱ ተመታ ፣ ቅስሙ ተሰበረ
ተስፋ ልጁን አጥቶ ፣ በቁጭት አረረ።
ጉልበቱ ሸብረክ አለ ፣ ወገቡ ተቀጨ
ገና ሳይፈተል ፣ ነጠላው ተቋጨ።

ወጣቶች እየዬ አሉ ፣ እናቶች ደረት መቱ
አባቶች ተከዙ ፣ እህቶች ዋተቱ
ተስፋዎች ጠወለጉ ፣ መንገዶች ራቁ
ጽሁፎች ደበዘዙ ፣ ቀለሞች ደረቁ
ክንዶችም ዛሉ ፣ አንደበቶች ተዋጡ
ጣቶችም ታጠፉ ፣ ዓይኖች ብርሃን አጡ
ጆሮ ጉዱን ሰማ
ከሕንፃው ከማማ
“ጀግና እራሱን ወ…ረ…ወ…ረ…፣
ሞተ አሉ ተ…ቀ…በ…ረ…።”
አንድ ልጇን አጣች ፣ ምድር በደም ታጥባ
ተስፋዬ ሞቶባት ፣ ስትጮህ ስታነባ።

መሠረተ ደሃ ለጭቁን የቆመ፣
ሀገር ያስቀደመ
ሕይወቱን ለትግል ፣ ዕውቀቱን ለትግል
አሳልፎ የሰጠ ፣ የዓላማ አክሊል
እኔስ ለኢትዮጵያ ፣ ለእምዬ ሀገሬ
ትምህርቴም ለእሷ ነው ፣ ለድሃው ገበሬ
ምሁር ለሕዝብ! ፣ ምሁር ለሀገር!
አርሶ ላስተማረኝ ፣ ያገሬ ባለሀገር
በላቡ ላስከበረኝ ፣ ለኢትዮጵያ ላብ አደር
አለብኝ ምከፍለው የትላንት፣
የአምናና ካቻምና ያላለቀ ብድር
ብሎ የተነሳ ፣ ተስፋዬ ተወለደ ከኢሮቦች መንደር።

እሱነቱን ለሕዝብ ፣ በደም የለወጠ
ለሰው ልጆች መብት ፣ ዕውቀቱን የሰጠ
የሕዝብን አደራ ፣ ለንዋይ ያልሸጠ
ለኢትዮጵያ ሀገራችን ፣ ዘብ ሆኖ የቆመ
ያ የጀግና ልጅ ፣ ከአሲምባ ያለመ
ከታጋዮች መሃል ፣ ገብቶ ያታገለ
ገብቶ የታገለ
በትግል መሞትን ፣ በተግባር ያሳየ
የትግል መምህር ፣ ይታወስ ተስፋዬ።

“ቢወቀጥ አጥንቴ ፣ ቢንቆረቆር ደሜ”
ታይቷል በተስፋዬ ፣ ለሀገር ልምላሜ
“ፍፁም ነው እምነቴ ፣ የትግሉ ነው ሕይወቴ”
እስከዘለዓለሙ ፣ ተጽፏል በደምህ
ሁሌም ይዘመራል ፣ በጀግና አንደበትህ።

ለአምባገነን መንግሥት ፣ ሕዝብን ላልወከለ
ሥጋህ አልተገዛም ፣ ሳለ እየታገለ
ጭራ ለቆሉቱ ፣ ለባንዳ ምሁራን
አርአያ ቴዎድሮስ ፣ አልሰጠህ እጅህን
በአጥንት በደምህ ፣ ጽፈሃል ታሪክን ።

ተስፋዬ ፦ የሀገር አበባ
የትግል ካባ
የጭቁን መምህር
የሕዝብ አምባሳደር
ሕይወትህ ላብ አደር
ኑሮህ ለአርሶ አደር
የምሁር አርአያ
ጽናትህ መለያ
ፍቅርህ ኢትዮጵያ።

አንት የትውልድ አውራ ፣ ስምህ ዳግም ያብራ
ተስፋህም ይለኮስ ፣ ይሁነን ደመራ
ገና ይቀርሃል ፣ መች ደረስህ ከግብህ
ይታፈስ ደምህ ፣ ይሰብሰብ አጥንትህ
ለኢትዮጵያ ሀገራችን ፣ ዘብ ይቁም መንፈስህ።
አጥንትህ ይሸከም ፣ መለያ ዓላማውን
ደምህም ያለምልም ፣ የሕዝብ አንድነትን
ተስፋዬ ተስፋ ሁነን
እኛስ አንቀላፋን . . .
እኛስ አንቀላፋን. . .
መንፈስህ ይ..ቀ..ስ..ቅ..ሰ..ን..።
ከ«ያ ትውልድ ተቋም»

ያ ትውልድ

The Generation